

ሥዕል 10፡- ኪዳነ ምሕረት (የምሕረት አማላጅ)

«አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት፤ አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ ተስፋው አንቺ ነሽ።»

(ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 71)

«በኀበ ኵሉ መካን ርእስት አንቲ። ወሥዑጥ ስምኪ በኀበ እግዚአብሔር፤ በቦታው ሁሉ አንቺ ርስት ነሽ። ስምሽም በእግዚአብሔር ዘንድ በማማለድ ሥልጡን ነው።»

(መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 49-51)



# ምዕራፍ አምስት

## 5. ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም ከነገረ ድኅነት ጋር ያለው ምሥጢራዊ ትሥሥር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ልዩ የሆነ የክብር ሥፍራ አላት። ስለሆነም በቤተ ክርስቲያናችን ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ቅድስት ድንግል ማርያም በሰማይም በምድርም ካሉ ፍጥረታት ሁሉ ይልቅ የከበረች በመሆኗ ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ቀዳሚት ሆና ትከበራለች፣ ትመሰገና ለች።(304) ይህንን አስመልክቶ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና «ለኪ ይደሉ ሰበሔ ወክብር እምኵሎሙ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር። ቃለ አብ መጽአ ወተሰብአ እምኔኪ። ... አድኃነ ነፍሳቲነ በምጽአቱ ቅዱስ፤ ድንግል ሆይ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ ክብር ላንቺ ይገባል። አካላዊ ቃል ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከሥጋሽ ሥጋ፣ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆነ። ... በልዩ አመጣጡ፣ በጽኑ ቀጠሮው ማለትም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም መጥቶ አዳነን»(305) በማለት ይመሰክራል።

---

(304) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ «መልክዐ ሥዕል» መጽሐፈ ሰዓታት፣ (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 266። Wondemagegnehu and Motovu eds., *The Ethiopian Orthodox Church,* 106-107. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of Jesus,* 14-15. Anthony, "Mary in the Orthodox Tradition," 95. O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary,* 381. አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም፣* ገጽ 48-49፣ 57።

(305) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 116-117። Abba Melketsedek, *The Teaching of the Ethiopian Orthodox Church,* 69-70. Daniel, *Blessed Virgin Mariam,* 118-119.

## 5.1 የዐሥራው መጻሕፍት ምስክርነት

እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆኑት መጻሕፍት አምላካውያት ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በድቀተ ኃጢአት ምክንያት በፍዳና በመርገም ተይዞ፣ በመንጸፈ ደይን ወድቆ፣ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ የነበረው መላው የሰው ዘር በሐዲስ ተፈጥሮ የዳነባትና አጥቶት የነበረውን አምላካዊ ጸጋና ክብርም ዳግመኛ የተጎናጸፈባት የሕይወት መሠረት፣ የድኅነት ምክንያት በመሆኗ ልዩ የክብር ሥፍራ እንዳላት በስፋት ይመሰክሩላታል:: ይልቁንም ሊቁ «በከመ አሰፈዎሙ ዲያብሎስ ከዊነ አምላክ ለአዳም ወለሔዋን ከማሁ አሰፈዋ ገብርኤል ለማርያም ወሊደ አምላክ በሥጋ»(306) ሲል እንደመሰከረው በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ ሆና ትከበራለች:: በመሆኑም ከዚህ ቀጥለን ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያምን አስመልክቶ ያላትን መጠነ ሰፊ አስተምህሮ የዐሥራው መጻሕፍትንና የመጻሕፍተ ቅዳሴያትን ምስክርነት መሠረት አድርገን ከነገረ ድኅነት ምሥጢር ጋር በማገናዘብ በዝርዝር እንመለከታለን::

### 5.1.1 መልዕልተ ፍጡራን፤ መትሕተ ፈጣሪ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መልዕልተ ፍጡራን (ከፍጡራን ሁሉ በላይ)፣ መትሕተ ፈጣሪ (ከፈጣሪ በታች) ሆና ትከበራለች:: በመሆኑም ለዚህ ልዩ ክብሯ መሠረቱ ወላዲተ አምላክነቷ፣ ዘለዓለማዊት ድንግል መሆኗና ይልቁንም ደግሞ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላት ታላቅና ልዩ የሆነ ሱታፌዋ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሏት መጠነ ሰፊ ውዳሴያትና ዝማሬያት ውስጥ ሁሉ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ተገቢውን ምስጋና ታቀርባለች:: የእመቤታችን ምስጋና ከሌሎቹ ቅዱሳን ምስጋና የበለጠና ልዩ የሚያደርገው ልዑለ ባሕርይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእርሷ የተሰጠው አምላካዊ ጸጋና ክብር ልዩ ስለሆነ ነው::(307)

(306) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 97::



ይህ ታላቅና ልዩ የሆነው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርና ውዳሴ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልቡና ውስጥ የጠለቀና ሥር የሰደደ ነው:: ይህም በዕለት ተዕለት መንፈሳዊ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ሁሉ በሰፊው የታወቀና የተረዳ ዘወትርም ጎልቶ የሚታይ ሕያው ምሥጢር ነው:: ስለሆነም «በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴያችን ሁሉ ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንዘምረው የድንግል ማርያምን ውዳሴ ነው::»(308) ለምሳሌ ያህል ብንመለከት «አቡነ ዘበሰማያት» ብለን የምስጋና ባለቤት የሆነውን ሰማያዊ አባታችንን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርን ካመሰገንን በኋላ ቀጥለን «በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ» ብለን ደግሞ እመቤታችንን እናመሰግናታለን::

ከዚህም ጋር በዘወትር ጸሎታችንም «ስብሐት ለአብ፣ ስብሐት ለወልድ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ» ብለን በአንድነት የሚቀደሰውን፣ በሦስትነት የሚሠለሰውን አምላክ ካመሰገንን በኋላ «ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ» ብለን ደግሞ እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን በደረጃው እናመሰግናታለን:: ከዚህም ሌላ ከሁሉ አስቀድመን «ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ» በማለት ስሙን ቀድሰን፣ ክብሩን እንወርስ ዘንድ በአርአያውና በአምሳሉ አልቆና አክብሮ የፈጠረንን ቅዱስ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: በመቀጠል ደግሞ «ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ» ብለን

(307) *ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣* «በእንተ ብሥራተ መልአክ»፣ *ሃይማኖተ አበው፣* ገጽ 252:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 380፣ 386:: አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣* ገጽ 155:: እንዱዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ «እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» *ፍሬ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ አምነዝሬት፣* ኅዳር 21/1997 ዓ.ም.፣ ገጽ 7:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 73, 83.

(308) አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣* ገጽ 131::

የባሕርያችን መመኪያ፣ የድኅነታችን መሠረት የሆነችውን ቤዛዊተ
ዓለም ቅድስት ድንግል ማርያምን እናመሰግናታለን። ለዚህም ምስጋ
ናችን አብነቶቻችንና ምስክሮቻችን ከሰማያውያን ቅዱሳን መላእክት
መካከል መልአከ ብሥራቷ የሆነው መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል
ሲሆን ከምድራውያን ቅዱሳንና ቅዱሳት መካከል ደግሞ መንፈስ
ቅዱስን የተመላች ቅድስት ኤልሳቤጥና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የከበረው
ልጇ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ነው።[309]

መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል ወላዲተ አምላክ ድንግል
ማርያምን ያሰማት ቃለ ብሥራትና ቃለ ፍሥሐ ጥልቅ የሆነ ልዩ
አምላካዊ ምሥጢር ያለው መሆኑ በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲ
ያናት መጻሕፍተ ውዳሴያትና ቅዳሴያት ውስጥ በስፋት ተገልጿል።
ስለሆነም መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን «ተፈሥሒ ኦ
ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ውዳሴ፣ ምል
ዕተ ክብር የሆንሽ ድንግል ሆይ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሥጋሽ
ሥጋ፣ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ከአንቺ በተዋሕዶ ሰው ሆኗልና ደስ
ይበልሽ» (ሉቃ. 1÷28) ሲል ያመሰገናት ምስጋና ከፍጡራን ወገን
ለማንም ያልቀረበና ወደፊትም የማይቀርብ ልዩ ምስጋና ነው። ከዚህም
ጋር በመልአኩ የተሰበከው ይህ ቃለ ፍሥሐ ለአምስት ሺህ አምስት
መቶ ዘመናት አዝኖና ተክዞ ይኖር ለነበረው መላው የሰው ዘር በእመቤ
ታችን በድንግል ማርያም አማካይነት የተላለፈ በመሆኑ የቤተ
ክርስቲያናችን መጻሕፍተ ውዳሴያት በመተባበር «ተፈሥሒ ኦ ሙኃዘ
ፍሥሐ፤ የተድላና ደስታ መፍሰሻ ሆይ ደስ ይበልሽ»[310] እያሉ ቤዛዊተ
ዓለም ድንግል ማርያምን ዘወትር ያመሰግኗታል፣ ያከብሯታል።

[309] McHugh, *The Mother of Jesus in the New Testament*, 37-43. Palmer, *Mary in the Documents of the Church*, 53-54, 108-109. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 53.

[310] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 29። *ድርሳነ ገብርኤል*፣ ገጽ 8-9፣ 20። አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ «እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል»፣ ገጽ 7። Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 11. Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion*, 6-10.



ቀደም ብለን በምዕራፍ ሁለት፣ ሦስትና አራት ላይ በስፋት
እንደገለጽነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከፍጡራን
ሁሉ ተለይታ ለአምላክ እናትነት፣ ለመለኮት ማደሪያነትና ለድኅነተ
ዓለም መሣሪያነት መመረጧን አውስተናል። ዳግመኛም በዚህ ልዩ
ጸጋዋ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን እንበለ ዘርዕ፣ እንበለ ሩካቤ በኀቱም
ድንግልና ፀንሳ፣ በኀቱም ድንግልና በመውለዷ ድንግል ወእም ማለትም እናት
ነትን ከድንግልና፣ ድንግልናን ከእናትነት ጋር አስተባብራና አንድ አድ
ርጋ ይዛ በከብረ ወሊድ ላዕለ ክብረ ድንግልናን ተጎናጽፋ የተገኘች ወትረ ድን
ግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን ተመልክተናል።

በዚህም መሠረት ረቂቅና ድንቅ የሆነውን ይህንን የመድኃ
ኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ድንግልናዊ ፅንስና ልደት በመግለጥ በቤተ
ክርስያናችን ዘወትር የሚዘመሩትና የሚጸለዩት የእመቤታችን ውዳሴ
ያት «... ወሶበ ርእዩ እግዚኦሙ ዘአስተጋብአ ኵሎ ፍጥረታተ እንዘ ይነብር ውስተ
ሕፅንኪ ወዘይሴሲ ለኵሉ ፍጥረት ይጠቡ ሐሊበኪ ከመ ሕፃን ...፤ ሰማያውያን
የሚሆኑ ቅዱሳን መላእክት ፍጥረታን ሁሉ በመሐል እጁ ሰብስቦ
የሚይዘውን ጌታ በአንቺ እቅፍ ውስጥ ሆኖ ባዩት ጊዜ፤ አንድም ፍጥ
ረታትን ሁሉ አስተካክሎ የሚመግበው ጌታ እንደ ሕፃናት ድንግልናዊ
ወተትን ያስገኙ ጡቶችሽን ይዞ ሲጠባ ባዩት ጊዜ ትሕትናውን
ፈጽመው አደነቁ»[311] በማለት በእርሷ ሕይወት የተፈጸመውን አምላካዊ
ድንቅ ምሥጢር ይመሰክራሉ።

በኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት እመቤ
ታችን ድንግል ማርያም የምትጠራባቸው ሦስት ዋና ዋና ስያሜዎች
አሏት። እነዚህም፦ ወላዲተ አምላክ [*Theotokos* - Mother of God]፣ ወት
ረ ድንግል (ዘለዓለማዊት ድንግል) [*Aeiparthenos* - Ever Virgin]፣ በአማን
ንጽሕት ወቅድስት በኵሉ [*Panagia* - All Pure and All Holy] ናቸው።

[311] ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 407። አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 657። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 206። Brock, *Bride of Light*, 58, 100. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 23-24. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 384።

ስለሆነም «የእምነት መመሪያ ሕግ የአምልኮና የጸሎት ሥርዓት መመሪያ ሕግ ነው» *["lex orandi, lex credendi"]*(312) በሚለው የሥነ መለኮት ሊቃውንት ዐቢይ መርሕ መሠረት እነዚህ የእመቤታችን ልዩ መጠሪያዎች በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን የቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናና ክብር ከሌሎች ቅዱሳንና ቅዱሳት ምስጋናና ክብር ሁሉ ይልቅ የተለየና የበለጠ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘወትር ሥርዓተ አምልኮዋ ለቅድስት ሥላሴ ብቻ የምታቀርበውን አምልኮት [Adoration]፤ እንዲሁም ለወላዲተ አምላክ ለድንግል ማርያም የምትሰጠውን አክብሮት [Veneration] በሚገባ ለይታና ጠንቅቃ ታስተምራለች። ስለሆነም ኦርቶዶክሳውያን የሥነ መለኮት ሊቃውንት የልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ፈጣሪነቱን፣ ሠራዒነቱን፣ መጋቢነቱን፣ መለኮታዊ ክብሩን፣ አምላካዊ ጥበቃውን፣ በሁሉ የመላ፣ ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ፣ ቅዱስና ንጹሐ ባሕርይ አምላክ መሆኑን በመግለጥ ለጌትነቱ የሚገባው ልዩ የባሕርይ ክብርና ምስጋና የሚቀርብበትን ሃይማኖታዊ ሥርዓት **አምልኮት** [*latreia* - adoration] ይሉታል። በአንጻሩ ደግሞ ምክንያተ ድኅነት ለሆነችው ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣት ልዩ ጸጋና ክብር መሠረት ተገቢው ምስጋና የሚቀርብበት ሥርዓት **አክብሮት** [*hyperduleia* - Veneration] ይባላል። ከዚህም ጋር ለቅዱሳን የሚሰጠው አክብሮት ደግሞ *[duleia /proskynesis]* በመባል ይታወቃል።(313)

(312) Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 382. Ware, *The Orthodox Church,* 257-258. Donald G. Dame, "From Dysfunction to Disbelief: The Virgin Mary in Reformed Theology," *Mary's Place in Christian Dialogue* ed., Alberic Stacpoole (Wilton, Connecticut: Morehouse-Barlow Co., Inc., 1983), 142-150. Tambasco, *What are they Saying about Mary?*, 65-66. Mascall, "The Mother of God," 180. Jaroslav, *Mary Through the Centuries: Her Place in the History of Culture,* 59. *ተአምረ ማርያም*፣ ገጽ 3-7።

(313) ሊቃውንት ጉባኤ (ምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት)፣ *ፍሬ ተዋሕዶ*፣ (አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 25-28። አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት*፣ 205-207። አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ*



## 5.1.2 አማናዊት ታቦተ ጽዮን፣ አማናዊት ኢየሩሳሌም

ቅዱሳት መጻሕፍት በዘመነ ብሉይ የነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት ለእስራኤል ዘሥጋ ሥርዓተ አምልኮ ሕይወታቸው ዋነኛው ማዕከል መሆኑን በስፋት ይገልጻሉ። ስለሆነም ሕዝበ እስራኤል በዘመነ ብሉይ በነበረችው በታቦተ ጽዮን አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር በአምልኮ፣ በጸሎትና በመሥዋዕት ዘወትር ይገናኙባት ነበር። የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ነገረ ማርያም አስተምህሮ የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክርነት መሠረት በማድረግ በብሉይ ኪዳን በነበረችው ታቦተ ጽዮንና በዘመነ ሐዲስ በተገለጠችው አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን በቅድስት ድንግል ማርያም መካከል ያለውን ረቂቅና ድንቅ ምሥጢራዊ ንጽጽር አምልቶና አስፍቶ ያስረዳል፣ ያስገነዝባል።

ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም ትምህርት በዚህ አንጻራዊ ትርጓሜ አማካይነት ከምድራውያንና ከሰማያውያን ፍጡራን ሁሉ በላይ የሆነውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ልዩ ንጽሕናና ቅድስና፣ ክብሯንና ልዕልናዋን በግልጥ ያስረዳል። ስለሆነም በድንግል ማርያምና በታቦተ ጽዮን መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና «ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ ዘገቡር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፤ ከማይነቅዝ እንጨት የተቀረጸ በውስጥ በአፍአ በወርቅ የተለበጠ ታቦት አንቺ ነሽ»(314) በማለት ይመሰክራል። በዚህ ቃለ ውዳሴ መሠረት ወላዲተ

*ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 155፣ 158። Ware, *The Orthodox Church,* 257. Mascall, "The Mother of God," 174. Wondemagegnehu and Motovou, *The Ethiopian Orthodox Church,* 21. John de Satgé, "The Bible and Tradition in Regard to the Blessed Virgin Mary," *Mary's Place in Christian Dialogue* (Wilton, Connecticut: Morehouse-Barlow Co., Inc., 1983.), 53. Dawe, "From Dysfunction to Disbelief: The Virgin Mary in Reformed Theology, 163.

(314) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 190-194። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 266። *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 3፣ 48። አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም*፣ ገጽ 49። Brock, *The Bride of Light,* 41.

አምላክ ድንግል ማርያም ከማይነቅዝ እንጨት በተቀረጸ ታቦት መመሰሏ ንጽሐ ጠባይዕ ሳያድፍባትና ቅድስና ባሕርይ ሳይጐድፍባት፣ በርእዩ (በማየት)፣ በሰሚዐ (በመስማት)፣ በገሢሥ (በመዳሰስ)፣ በአጼንዎ (በማሽተት) ምክንያት አንዳችም እድፍ ጉድፍ ሳያገኛት በንጽሕና በቅድስና ጸንታ በኃጢአት ሳትለወጥ ለመኖሯ ምሳሌ ነው:: ይህንንም መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን «አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ፤ ምክንያታዊ ነውረ ኃጢአት የሌለብሽ፣ የኃጢአት ሽታ ያልደረሰብሽ ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና አንቺ ነሽ» (መኃ. ሰሎ. 4÷7) ሲል በምሥጢር ተናግሮላታል::

ዳግመኛም ታቦተ ጽዮን በከበረ ወርቅ መለበጧ አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን እመቤታችን በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና የተሸለመችና ያጌጠች መሆኗን በምሥጢር ያጠይቃል:: በተጨማሪም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በሐልዮ (በማሰብ)፣ በነቢብ (በመናገር)፣ በገቢር (በመሥራት) ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ፍጽምት፣ ኅትምት እንደሆነች በመግለጥ በዚህ ልዩ ጸጋዋ ከልዑላን ቅዱሳን መላእክትና ከትሑታን ደቂቀ አዳም ሁሉ ይልቅ የተለየችና የከበረች መሆኗን በምሥጢር ያሳያል:: ስለሆነም እመቤታችን በዚህ መዓዛ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ ለወልደ እግዚአብሔር ማደሪያነት መብቃቷንና ለድኅነተ ዓለም መሣሪያነት መመረጧን ይገነዘቧል::(315)

Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," 16. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር*፣ *["The Book of Mystery"]*፣ *CSCO*, ገጽ 373:: Carol, *Mariology* vol. 1, 17. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 157.

(315) ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ [Emperor Zara Yacob]፣ *መጽሐፈ ብርሃን*. *["The Book of Light"] CSCO*, 223. አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 609:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 134፣ 282-283:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 190-194:: *ተአምረ ማርያም*፣ ገጽ 4-5:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 3-5. ሊቃውንት ጉባኤ (ምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት)፣ *ፍሬ ተዋሕዶ*፣ ገጽ 49::



ከዚህም ጋር ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይህን ምሥጢር አራቆ ሲተረጉም:-

> ሰሙትኪ ይቤሉ እግዚአብሔር ግበር ለከ ታቦተ እንተ ዕፅ ወትቀፍኣ በወርቅ ንጹሕ እንተ ዕፍእሃ ወእንተ ውስጣ ወትደይ ውስቴታ ትእዛዘ ዘአሁበከ ሀሎ:: ... ከማሁ አስተዳለዋ ለድንግል ከመ ትኩን ሥርጉተ በቅድስና ወበንጽሕ:: ... ወለዝሰ ይትመየጥ ፍካሬሁ ኀበ ድንግል እንተ ውስጣ ዘይቤ በደዋሂ ወበልቡና:: ወእንተ አፍኣሃሰ ዘይቤ በጾም ወበጸሎት ወበንጽሐ ሥጋ ዘይኤድሞ ለመንፈስ ቅዱስ»(316)

በማለት መስክሮላታል::

ከላይ የገለጥነውንና ከፍጡራን ሁሉ በላይ የሆነውን የወላዲተ አምላክን ንጽሕናና ቅድስና አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ [St.Jacob of Serug (A.D. 451-521)] እንዲሁም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በአንድነት ሲገልጹ አማናዊቷን ታቦተ እግዚአብሔር ድንግል ማርያምንና የቃል ኪዳኑን ታቦት በማነጻጸር በስፋት አስረድተዋል:: እኒህ ቅዱሳን አበው እንዳስተማሩት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ መኖሯ ሁለንተናዋ በወርቅ የተለበጠው ታቦተ ጽዮን በልዑል እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከመቀመጧ ጋር በምሥጢር የተያያዘ ከመሆኑም ሌላ አማና ዊቷ ታቦተ ጽዮን ድንግል ማርያም በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ፍጽምትና ኅትምት መሆኗንም ይመሰክራል::(317)

ከዚህም ጋር ታቦተ ጽዮን የቃለ እግዚአብሔር ማደሪያ እንደሆነች፤ አማናዊቷ ታቦት ቅድስት ድንግል እመቤታችንም ለአካላዊ ቃል ለእግዚአብሔር ወልድ ማደሪያው ሆናለች:: ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ይህንን አማናዊ ፍጻሜ ምሥጢር በመግለጥ ወላዲተ

(316) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 373-374::

(317) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 74. ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 404:: Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 24-25.

አምላክን ባመሰገነበት ውዳሴው ሲናገር “ኮንኪ ታቦተ ለፈጣሬ ሰማያት ወምድር። ፃርኪዮ በከርሥኪ ተሰዓተ አውራኃ። አንቲ ማእምንት ለዘኢያገምርዎ ሰማያት ወምድር፤ ድንግል ማርያም ሆይ ሰማይና ምድርን ለፈጠረ አምላክ ለእርሱ ማደሪያ ሆንሽ። ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንሽ ቻልሽው፣ ተሸከምሽው። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን ለመወሰን የታመንሽ አንቺ ብቻ ነሽ”[318] በማለት መስክሮአል።

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ነቢዩ ኢሳይያስ ሀገረ ሰላም፣ ሀገረ እግዚአብሔር ከሆነችው ከኢየሩሳሌም ቃለ እግዚአብሔር እንደሚገኝ ተናግሮአል። በአንጻሩ ደግሞ ከአማናዊቷ ኢየሩሳሌም ከቅድስት ድንግል ማርያም ቃለ አብ ሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተወልዶ ተገልጦባታልና እመቤታችን በምሥጢር ኢየሩሳሌም ትባላለች። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ “ቃል ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ” (ዮሐ. 1÷14) ሲል እንደመሰከረ። ከላይ እንደገለጥነው ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ ሰላም፣ ሀገረ እግዚአብሔር፣ ማኅደረ እግዚአብሔር ማለት ነው። አማናዊቷ ኢየሩሳሌም ቅድስት ድንግል እመቤታችንም ንጉሠ ሰላም የሆነው ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረባትና የነገሠባት ሀገሩ፣ ማኅደሩ ናት።

የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍተ ውዳሴያት “ብኪ ድኅነ ዓለም፣ ወበወልድኪ ኮነ ሰላም፤ ድንግል ማርያም ሆይ በአንቺ ምክንያትነት ዓለም ዳነ፣ በልጅሽም ፍጹም ሰላም ሆነ፣ ተደረገ”[319]፤ “ዛቲ ይእቲ ኢየሩሳሌም ሀገሮሙ ለነቢያት፤ የቅዱሳን ነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ይህቺ እመቤታችን ናት”[320] በማለት እመቤታችን ሀገረ ሰላም መሆኗን አስረግጠ ተናግሮአል። ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያም በመልእክቱ “እርሱ ሰላማችን ነውና” (ኤፌ. 2÷14-15) ሲል ከአማናዊቷ ሀገረ ሰላም ከድንግል

[318] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 164። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ [Emperor Zara Yacob], መጽሐፈ ብርሃን ["The Book of Light"], CSCO, ገጽ 67።

[319] መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 436።

[320] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 110።



ማርያም የተወለደውና ሰው የሆነው አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰላም፣ አምላከ ሰላም መሆኑን አስረግጦ ተናግሮአል። (ማቴ. 10÷12-13፤ ዮሐ. 14÷27፤ ዮሐ. 20÷19፣ 26)

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ እግዚአብሔር፣ ማኅደረ እግዚአብሔር ማለት ነው። አማናዊቷ ኢየሩሳሌም ድንግል ማርያምም እሙ እግዚአብሔር ጸባዖት፣ ማኅደረ መለኮት፣ መዝገበ ቃልናትና በምሥጢር ኢየሩሳሌም ትባላለች። ይህንን አስመልክቶ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሲናገር “ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔር ሀገር ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ እነሆ ስለ አንቺ የተነገረው ድንቅ ድንቅ ነገር፤ አንድም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ወልድ እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ በኀቱም ድንግልና ፀንሰሽ፣ በኀቱም ድንግልና እንድትወልጂው ያደረገበት ኃይሉና ጥበቡ ምንኛ ዕፁብ ድንቅ ነው”[321] (መዝ. 86÷3) በማለት አድንቋል። ይህ ልዩ አምላካዊ ምሥጢር የተፈጸመባት አማናዊቷ ሀገረ እግዚአብሔር እመቤታችንም በምስጋና ጸሎቷ “ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ... እስመ ገብረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ (ሉቃ. 1÷47፣ 49)፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና ማለት በኀቱም ድንግልና ፀንሼው፣ በኀቱም ድንግልና እንድወልደው አድርጎኛልና ሰውነቴ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች፣ ታመሰግነዋለች፣ ከፍ ከፍም ታደርገዋለች” ስትል መስክራለች።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕመ ፍቅሯና ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም ወላዲተ አምላክን ባመሰገነበት ውዳሴው “ኦ ማርያም ወላዲተ አምላክ ሀገር መንፈሳዊት ዘኃደረ ላዕሌሃ እግዚአብሔር ልዑል፤ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ ልዑል እግዚአብሔር ያደረብሽና የከተመብሽ ረቂቅ ከተማ ነሽ ሲል ተናግሮላታል። ይኸውም ንጉሥ በከተማው እንዲኖር፤ በባሕርዩ

[321] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 432።

ሞት፣ ሽረት፤ በመንግሥቱ ኅልፈት፣ ውላጤ የሌለበት ሰማያዊውና ዘላለማዊው ንጉሥ ክርስቶስም ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማኅፀኗን ዓለም አድርጎ በተዋሕዶ አድሮባታልና ሊቁ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሀገረ እግዚአብሔር ብሏታል::»(322)

ከዚህም ሌላ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "ፈለግ ዘይውኅዝ ያስተፌሥሐ ሀገረ እግዚአብሔር፤ የወንዝ ፈሳሽ የእግዚአብሔርን ሀገር፣ የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛታል" (መዝ. 45÷4) ሲል ተናግሮአል:: የዚህ ቃለ ትንቢት ትርጓሜ ለጊዜው በፈቃደ እግዚአብሔር ከሰማይ ታዞ የሚመጣ ዝናብ ሀገረ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ደስ ያሰኛታል ማለት የዘሩባትን እንድታበቅል፣ የተከሉባትን እንድታጸድቅ ያደርጋታል ማለት ነው:: ምሥጢራዊ ፍጻሜው ግን ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ከሰማይ የወረደው መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል አማናዊት ሀገረ እግዚአብሔር ድንግል ማርያምን "ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ውዳሴ፣ ምልዕተ ክብር ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ:: ልዑል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና (ከሥጋሽ ሥጋ፣ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ ይወለዳልና) ብሎ፤ አንድም "ትጸንሲ ወትወልዲ ወልደ" ብሎ እመቤታችንን ፈጽሞ ደስ ያሰኛታል ማለት ነው::(323) በዚህም ትርጓሜ ምሥጢር መሠረት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አማናዊት ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗን ይገነዘቧል::

## 5.1.3 የታቦተ ጽዮንና የአማናዊቷ ታቦት የእመቤታችን ምሥጢራዊ ንጽጽር

ቀደም ብለን በክፍል 5.1.2 ላይ በገለጥነው መሠረት በታቦተ ጽዮንና በአማናዊቷ ታቦተ ጽዮን በድንግል ማርያም መካከል ያለውን

(322) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 154::
(323) መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 248::



ሰፊና ጥልቅ ምሥጢራዊ ንጽጽር በዝርዝር እንመለከታለን:: ለዚህ አንጻራዊ ትምህርታችን መነሻ የምናደርገው በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ. 2÷3 ላይ "ሕግ ይወፅእ እምጽዮን ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም፤ ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣል" ሲል ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ የመሰከረውን ኃይለ ቃል ነው:: ይህ ታላቅ ቃለ ትንቢትና ቃለ ተስፋ ከዐበይት ነቢያተ እስራኤል መካከል አንዱ የሆነው ልዑለ ቃል ኢሳይያስ ስለ ጽዮን ክብርና ምንነት የተናገረው፤ እንዲሁም ስለ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ታላቅነትና ገናንነት የመሰከረው አማናዊ ቃለ ጽድቅ ነው:: ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ፣ በተሰጠው ሀብተ ትንቢት ተመርቶ የተናገረው ይህ ቃለ ትንቢትና ቃለ ተስፋ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሠራዔ ሕግ (የሕግ መገኛ) የሆነችውን ጽዮንን የሕዝብና የአሕዛብ መመኪያ እንደሚያደርጋት የሚያረጋግጥ የበረከት ቃል ነው::

በመሆኑም ይህ ታላቅ ቃለ ትንቢት ለጊዜው እስራኤል ዘሥጋ የሚጠበቁበትና የሚከብሩበት ሕግ የተገኘባትንና የተሰጠባትን ታቦተ ጽዮንን የሚያመለክት ሲሆን፤ ፍጻሜ ምሥጢሩ ግን ሠራዔ ሕግ (ሕግን የሠራ)፣ ሐጋጌ ሕግ (ሕግን የደነገገ፣ የሕግ ባለቤት) የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኋለኛው ዘመን ማለትም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው ሆኖ የተገለጠባትንና አማናዊት ጽዮን የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ያሳያል:: ምክንያቱም ጽዮን ማለት ትርጉሙ አምባ፣ መጠጊያ፣ መሸሸጊያ ማለት እንደሆነ ሁሉ (2ኛ ሳሙ. 5÷1-10)፤ አማናዊት ጽዮን የተባለችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም ጸወነ ሥጋ፣ ጸወነ ነፍስ ናትና፤ አንድም ጸወነ ጻድቃን ጸወነ ኃጥአን ናትና ነው:: ይህንን አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት፤ አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ ተስፋው አንቺ ነሽ»(324) በማለት ቤዛዊተ ዓለም

(324) ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 71-73::

ድንግል ማርያም ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፉ ምክንያት ከፈጣሪው አንድነት ተለይቶ፣ ልጅነቱን አጥቶ፣ ከክብር ቦታ ከገነት ወጥቶ ለነበረ አዳም መጠጊያው፣ መሸሸጊያውና ተስፋ ስንቁ መሆኗን ገልጾ መስክሮአል::

እንግዲህ እመቤታችን ድንግል ማርያም አማናዊት ጽዮን፣ አማናዊት ኢየሩሳሌም፣ አማናዊት ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗን በመግለጥ በመጠኑ ይህን ያህል ካልን ወደ ርእሰ ነገራችን ተመልሰን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምና በታቦተ ጽዮን መካከል ያለው ምሥጢራዊ ግንኙነትና ትሥሥር ምንድን ነው? ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንስ በየዓመቱ ኅዳር 21 ቀን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓትና በከፍተኛ ድምቀት የምታከብረውን የእመቤታችንን በዓል "ኅዳር ጽዮን" (በዓለ ጽዮን) ብላ መሰየሟ ምሥጢራዊ ትርጓሜውና ምክንያቱ ምንድን ነው? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መነሻ አድርገን ምሥጢራዊ ንጽጽሩን ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን::

በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት እንደተገለጸው በዘመነ ሐዲስ በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን የተፈጸመው የድኅነተ ዓለም ተስፋ (ሐዲስ ተፈጥሮ) እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ እንዲያው በድንገት ወይም በቅጽበት የተከናወነ አይደለም:: ይልቁንም ከሥጋዌው አስቀድሞ በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል በተገለጠውና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት በተነገረው ተስፋ ድኅነት መሠረት የተፈጸመ አምላካዊ የቸርነት ሥራ እንጂ:: ይኸውም ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ... በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" (ዕብ. 1÷1-2) ሲል እንደመሰከረው ነው::



ስለሆነም የአዲስ ኪዳኗ አማናዊት ታቦተ ጽዮን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብሉይ ኪዳን ከተመሰለችባቸውና ከተገለጠችባቸው አያሌ ዐበይት ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት መካከል አንዱና ዋነኛው ታቦተ ጽዮን ናት:: መጽሐፍ "ለእመ ኢተሰንአ ብሉይ ወሐዲስ በእንተ ማርያም ወበእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ርእዩ ከመ ይነግር ቀዳሚ በእንተ ደኃራዊ ወደኃራዊ ይፌጽሞ፤ ብሉይና ሐዲስ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያምና ስለ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት ተባብረው እንደተናገሩና እንደመሰከሩ እወቁ፤ ዳግመኛም ብሉይ ኪዳን ስለ አዲስ ኪዳን እንደሚናገርና እንደሚመሰክር፤ አዲስ ኪዳንም ብሉይ ኪዳንን እንዲተረጉመው፣ እንዲፈጽመው፣ እንዲያጸናው እዩ፣ ተመልከቱም"(325) እንዳለ በአዲስ ኪዳን የተከናወነው አማናዊ ምሥጢር ሁሉ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ መሆኑን ይመሰክቷል::

ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ በዘመነ ብሉይ ስለ ነቢዩ ኤልያስ የተነገረው ቃለ ትንቢት በዘመነ ሐዲስ በቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ተፈጽሟል:: ይህንን አስመልክቶ በቅዱስ ወንጌል እንደተገለጸው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር "ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ፤ ልትቀበሉትስ ብትወዱ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው" (ማቴ. 11÷13-14፤ 17÷10-13፤ ሚል. 4÷5) በማለት ተናግሮአል:: በዚህ መሠረት ኤልያስ ተብሎ የተነገረው በዮሐንስ እንደተፈጸመ ሁሉ፤ እንደዚሁም ጽዮን ተብሎ የተነገረው በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ተፈጽሟል:: (2ኛ ሳሙ. 6÷1-23፤ ሉቃ. 1÷26-56)

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በዘጸአት 40÷34 ላይ "ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ" ሲል

(325) Getachew Haile (Professor). *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 100-102. McHugh, *The Mother of Jesus in the New Testament*, 56-63. John Saward, *Redeemer in the Womb* (San Francisco: Ignatius Press, 1993), 29. Daniel, *Blessed Virgin Mariam*, 5. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 131-132::

በቅድስት ኦሪት የመሰከረውን፤ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ኃይለ ቃሉን በምሥጢር አገናኝቶ ሲናገር "ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ ... መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል÷፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ..." (ሉቃ. 1÷28፣ 35) ብሏል:: በዚህም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ውዳሴ፣ ምልዕተ ክብር የሆነች አማናዊት ድንኳን መሆኗን ይገነዘቧል:: ሊቁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት በመልክዐ ማርያም ድርሰቱ "ኦሙ ኃደረ ባዕቤኪ ፀሐየ ቅዱሳን ዘሬማ፣ ኃይለ ልዑል ጸለለኪ በመንክር ግርማ፤ ድንግል ሆይ በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራውና ለቅዱሳን ብርሃን፣ ዕውቀት የሆነው አማናዊው ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅፀንሽ ባደረ ጊዜ የልዑል እግዚአብሔር ኃይል በሚያስደንቅ ግርማ ከለለሽ፣ ጋረደሽ"[326] በማለት በአጽንኦተ ቃል አስረድቷል:: (ሥዕል 8 ይመልከቱ)

በዘመነ ኦሪት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሕዝበ እስራኤል ጋር የሚገናኝባትና በረድኤት የሚያድርባት ደብተራ ኦሪት (የመገናኛው ድንኳን) በዘመነ ሥጋዌ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ እስራኤል ዘነፍስ ከተባሉ ምእመናን ሐዲስ ጋር የተዋሐደባት፣ በረድኤት ያይደለ በኩነት ያደረባት የአማናዊቷ ድንኳን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት:: እስራኤላውያን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በብሩህ ደመና መታየቱንና አምላካዊ ክብሩም በደብተራ ኦሪት ላይ መገለጡን "ሸኪናኽ" ይሉታል:: ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አማናዊት ድንኳን መሆኗን ሲመሰክር "አንቲ ውእቱ ደብተራ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን፤ ድንግል ሆይ ሕግ የተጻፈበት ኪዳን ያለብሽ ከተለዩ የተለየሽ፣ ከከበሩ የከበርሽ፣ ቅዱሳን፣ ካህናት፣ የሚያገለግሉብሽ ድንኳን አንቺ ነሽ:: ...፤ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወኃደረ ኀበ ማርያም ድንግል፤ ይኸውም ሰው ሆኖ በማኅፀንሽ ያደረው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"[327]

[326] ዐዲ ዘርዐ ያዕቆብና ዐዲ ናዖድ፣ "መልክዐ ማርያም"፣ ገጽ 533-534::

[327] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 173-174፤ 183-184:: ቅዱስ ያሬድ፣



በማለት ተናግሮአል:: ከዚህ ቃለ ውዳሴ እመቤታችን ድንግል ማርያም ትስብእትና መለኮት የተገናኙባት፣ የተዋሐዱባትና አንድ የሆኑባት፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር የሆነች አማናዊት ድንኳን መሆኗን በምሥጢር እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::[328]

ሌላው ደግሞ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በጸጋ የሚያድርባትና በረድኤት የሚገለጥባት ታቦተ ጽዮን ከአሚናዳብ ቤት ወጥታ ወደ ዳዊት ከተማ በመጣች ጊዜ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በፍጹም ትሕትና ሆኖ "የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ይመጣል?" (2ኛ ሳሙ. 6÷9) በማለት ተናግሮአል:: ይህም በኋለኛው ዘመን ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ውዳሴ፣ ምልዕተ ክብር የሆነችው አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን እመቤታችን ድንግል ማርያም ወደ ካህኑ ዘካርያስ ቤት በገባችና ቅድስት ኤልሳቤጥን በጎበኘቻት ጊዜ ቅድስት ኤልሳቤጥ "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?" (ሉቃ. 1÷43) ስትል ከተናገረችው የትሕትና ቃል ጋር በምሥጢር የተወራረሰና የተገናዘበም ነው::

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በታቦተ ጽዮን ፊት ራሱን በትሕትና እንዳዋረደ ሁሉ፤ ቅድስት ኤልሳቤጥም ረቂቅና ጥልቅ የሆነውን ሰማያዊና መለኮታዊ ምሥጢር የሚገልጥ ከሣቴ ምሥጢር መንፈስ ቅዱስ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር ስላስረዳት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ "ምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ፤ የጌታዬ፣ የፈጣሪዬ እናቱ እመቤቴ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ

መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 383:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *ዕንዚራ ስብሐት ["The Lyre of Glory"] CSCO*, ገጽ 53:: Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 30. Brock, *The Bride of Light*, 25. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 75.

[328] Robert Payesko, *The Truth About Mary: A Scriptural Introduction to the Mother of Jesus for Bible-Believing Christians* vol. I (Santa Barbara, CA: Queenship Publishing (Company, 1996), 1-xviii- 1-xix. Russell, "The Blessed Virgin Mary in the Bible: The Scriptural Basis of Ecumenical Dialogue," 46. Laurentin, *Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 24-25, 30. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 92፣ 381::

ምንድን ነኝ?» (ሉቃ. 1÷43) ስትል በፍጹም ትሕትና ራሷን ዝቅ አድርጋ ተናግራለች::[329] ልጇ ቅዱስ ዮሐንስም ይህን የእናቱን ትሕትና አብነት አድርጎ ፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርሱ ሊጠመቅ በመጣ ጊዜ:- «እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል:: አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?» (ማቴ. 3÷13-14) ሲል በፍጹም ትሕትና መልሷል::

ከዚህም ጋር በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 6÷14-15 ላይ «ዳዊትም በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘፍን (ያመሰግን፣ ይዘምር) ነበር፤ ... ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ ሆ እያሉ ቀንደ መለከትም እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት አመጡ» በማለት ነቢየ አምላክ የሆነው ንጉሠ እስራኤል ዳዊት የልዑሉ ባሕርይ እግዚአብሔር ማደሪያና መገለጫ ለሆነችው ለታቦተ ጽዮን ክብር ሁለንተናዊ ሕይወቱን እንደሰጠ ያስገነዝበናል:: በአንጻሩም ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ «ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ጽንሱ በማኅፀኗ ውስጥ ዘለለ» (ሉቃ. 1÷41-44) ሲል ጸያሔ ፍኖት (የጌታ መንገድ ጠራጊ) የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ወዝገበ ቃለ ወማኅደረ መለኮት ለሆነችው ለአማናዊቷ ታቦተ ጽዮን ለቅድስት ድንግል ማርያም በደስታ አሸበሸበ፣ ሰገደ ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል::

የአዲስ ኪዳን ሊቃውንትም ወንጌላዊው «ዘለለ» ያለውን ገጸ ንባብ በምሥጢር ወስደው «ዮሐንስ ሰገደ ውስተ ከርሠ እሙ፤ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የእናቱን የቅድስት ኤልሳቤጥ ማኅፀን ቤተ መቅደስ አድርጎ በማኅፀኗ ድንግል ላደረው አምላክ የባሕርይ (የአምልኮ) ስግደት ሰገደ፤ መዝገበ ቃል፣ እመ አምላክ፣ መንበረ መለኮት ለሆነችው ለአማናዊቷ ታቦት ለድንግል ማርያም ደግሞ በጸጋ ሰገደ»[330] ብለው ተርጉመውታል::

[329] Saward, *Redeemer in the Womb*, 23-33. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 55. Payesko, *The Truth About Mary*, 1-xix - 1-xx. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 31. Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion*, 10. Jim Forest, *Praying with Icons* (Maryknoll, New York: Orbis Books, 1997), 26.

[330] ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 3::



በመሆኑም ዛሬ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ከማኅፀነ ጥምቀቷ ተወልደን፣ መንፈስ ልደትን አግኝተን፣ ከሐሊበ ጸጋዋ ተመግበን በጸጋ መንፈስ ቅዱስ በከበርንባት እናታችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነን የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ውዳሴዋንና ተአምሯን፣ ክብሯንና ልዕልናዋን፣ በመስማት ፍጹም መንፈሳዊ ደስታን ተሞልተን የምናከብራት፣ የምንዘምርላትና የምንሰግድላት መንፈስ ቅዱስን የተመላ ቅዱስ ዮሐንስንና ልበ አምላክ የተባለው ቅዱስ ዳዊትን አብነት አድርገን መሆኑን ይመሰክቷል::[331]

ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን አባት ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኤልሳቤጥን እንደጎበኘቻት የሚያወሳውን ገጸ ንባብ በተረጎመበት የነገረ ማርያም የምሥጢር መድበሉ ሲናገር «ንጋትና ምሽት ተገናኙ» ብሏል:: በመቀጠልም ይኸው አባት ሲያብራራ ንጋት የተባለችውና በንጋት የተመሰለችው በድቅድቅ ጨለማ ኃጢአት ተውጦ ለነበረው ዓለም አማናዊውን ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን (ሚል. 4÷2፤ ማቴ. 17÷2) ወልዳ ያስገኘችው አማናዊት ምሥራቀ ፀሐይ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መሆኗን መስክሮአል::[332] ዳግመኛም ይኸው ሊቅ ቅድስት ኤልሳቤጥን በምሽት የመሰላት ትምህርቱና ሕይወቱ እንደ ጨረቃ ብርሃን የነበረውን መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ስላስገኘች ነው:: ይህንንም ጌታችን በወንጌለ መንግሥቱ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ሲናገር «እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ÷ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ» (ዮሐ. 5÷35) በማለት ተናግሮለታል::

ከላይ የገለጥነው ምሥጢር ቅዱስ አባ ሕርያቆስ «**አብ ፀሐዩ፣ ወልድ ፀሐዩ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሐዩ:: አሐዱ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘላዕለ ኵሉ፤**

[331] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 135-136፣ 225:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 7:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 190-194:: Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 37.

[332] St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 49.

አብ ፀሐይ ነው፣ ወልድ ፀሐይ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ነው:: ለሁሉ የሚያበራ አንድ የእውነት ፀሐይ ነው:: ዳግመኛም ... አብ ኀሒ፣ ወልድ ኀሒ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ኀሒ፤ አብ ኀሒ ነው፣ ወልድ ኀሒ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ኀሒ ነው:: አሐዱ ውእቱ ኀሒ ጽግሕ ዘበጸዳለ ብርሃኑ ሰሰለ ጽልመት፤ በሥልጣኑ ኦሪት ያለፈችበት፣ ኃጢአት ድንቁርና የጠፋችበት ብርሃንነት ያለው አንድ ኀሒ ነው»[333] ብሎ ከተናገረው ኃይለ ቃል ጋር በምሥጢር የተገናዘበና የተሰናሰለም ነው::

በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምና በታቦተ ጽዮን መካከል ያለው ሌላው ምሥጢራዊ ንጽጽር ደግሞ በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 6÷11 ላይ «የእግዚአብሔር ታቦት በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ያህል ተቀመጠ፣ እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ» ይላል:: የድኅነተ ዓለምን ዜና ምሥራች ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያበሥረው ቅዱስ ወንጌል የዚህን አማናዊ ምሳሌ ምሥጢራዊ ፍጻሜ ሲያስረዳ «ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርስዋ (በኤልሳቤጥ) ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤቷም ተመለሰች» (ሉቃ. 1÷56) በማለት በግልጥ ይመሰክራል::

እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን የልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ማደሪያ የሆነችው ታቦተ ጽዮን ለአቢዳራ ቤት በረከት ምክንያት እንደሆነች ሁሉ፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጠው አማናዊቷ ጽዮን እመቤታችንም ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በመጣችና በጎበኘቻት ጊዜ ወንጌላዊው «ወመልዓ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኤልሳቤጥ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት» (ሉቃ. 1÷41) እንዳለ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተመልታለች፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን አግኝታለች::

ይልቁንም ደግሞ መዝገበ በረከት የሆነችው ድንግል ማርያም ኤልሳቤጥን ከጎበኘቻት በኋላ «የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ÷

[333] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 146-147::*



ወንድ ልጅም ወለደች:: ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ደስ አላቸው::» (ሉቃ. 1÷57-58) ብሎ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው ቅድስት ኤልሳቤጥ ፍጹም የሆነ ተድላና ደስታን የሚሰጥ ፍሬ በረከት ቅዱስ ዮሐንስን አግኝታለች:: ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ይህ ፍሬ በረከት የልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አምላካዊ ጸጋ መሆኑን ሲገልጥ «እነሆ÷ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው» (መዝ. 126÷3) በማለት አስረግጦ ተናግሯል:: በሌላ አገላለጽ የታቦተ ጽዮን በቤተ አቢዳራ መቀመጥ በአቢዳራ ሁለንተናዊ ሕይወት በረከትን እንዳስገኘ ሁሉ፤ የአማናዊቷ ጽዮን የድንግል ማርያም በቤተ ዘካርያስ መገኘት ልዩ ጸጋንና በረከትን አስጥቷል፤ ፍጹም የሆነ ደስታንም አስገኝቷል::[334]

ቅድስት ድንግል እመቤታችን በታቦተ ጽዮን የመመሰሏን ምሥጢር የተለያዩ ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳት ሥዕላት በግልጽ ያስረዳሉ:: ለምሳሌ ያህል ብንመለከት በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት የሚሣለው «ምስለ ፍቁር ወልዳ፤ እመቤታችን ከተወዳጅ ልጇ ጋር» ተብሎ የሚታወቀው የእመቤታችን ሥዕል በግራና በቀኝ መልአከ ብሥራቷ ቅዱስ ገብርኤልና መልአከ ዑቃቢዋ /ጠባቂዋ/ ቅዱስ ሚካኤል በክንፎቻቸው እንደከለሏትና እንደጋረዷት ያሳያል:: የዚህ ሥዕል ምሥጢራዊ ትርጓሜው አማናዊቷ ታቦት ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዘመነ ብሉይ በቤተ መቅደስ ውስጥ በነበረችውና በሁለቱ ሥዕለ ኪሩብ ክንፎች ተጋርዳና ተከልላ በታየችው በታቦተ ጽዮን መመሰሏን በጉልህ ያመለክታል::[335] (ዘጸ. 25÷18-22)

[334] St. Jacob of the Serug, *On the Mother of God*, 53. *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 330-331:: *Laurentin, The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin,* 33-35.

[335] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ «መልክዐ ሥዕል»፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 258፣ 261:: አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣* ገጽ 120:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 194:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha] *ዕንዚራ ስብሐት* *["The Lyre of Glory"] CSCO*, 3. Getachew Haile

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ታቦተ ጽዮን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በረድኤት በሚያድርባትና በሚገለጥባት በቤተ መቅደስ ውስጥ እንደተቀመጠች፤ እንዲሁም አማናዊት ታቦት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ንጽሕተ ንጹሐን፣ ቅድስተ ቅዱሳን በመሆኗ በንጽሕና፣ በቅድስና፣ በድንግልና ጸንታ በቤተ መቅደስ ኖራለች::[336] ይህንን አስመልክቶ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እመቤታችንን ባመሰገነ በት ውዳሴው ሲናገር «... ዘነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ከመ ታቦት ዘግቡር ስሙዕ ዘኢይነቅዝ፤ ሥርግው በወርቅ ንጹሕ ወስቡጥ በዕንቁ ባሕርይ ዘዮንቱ ዘብዙኅ ሤጡ ከመ ዝ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ፤ አምላክን የወለድሽ እመቤ ታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከማይነቅዝ እንጨት እንደተቀረጸ፣ ዋጋው እጅግ ብዙ በሆነና በከበረ ወርቅ እንደተለበጠና እንዳማረ ታቦት በቤተ መቅደስ ኖርሽ»[337] በማለት በምሥጢር ተርጉሞና አራቆ አመስግኗታል:: (ሥዕል 8 ይመልከቱ)

ቅዱሳት መጻሕፍት በዘመነ ብሉይ የነበረው የአሚናዳብ ልጅ ዖዛ እጁን በታቦተ ጽዮን ላይ በድፍረት በመዘርጋቱ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደነደደበትና ስለ ድፍረቱም በዚያው በታቦቱ አጠገብ እንደተ ቀሰፈ በግልጽ ይመሰክራሉ:: (2ኛ ሳሙ. 6÷7፤ 1ኛ ዜና 13÷9-11) በዘመነ ሐዲስ ደግሞ አማናዊቷ ጽዮን እመቤታችን ድንግል ማርያም ከዚህ ዓለም ወደማያልፈው ዓለም በክብር በተሸጋገረችበት በዕለተ ዕ ረፍቷ ወቅት ቅዱሳን ሐዋርያት ሥጋዋን በጸሎትና በማዕጠንት አክብ ረው ለመሸኘት በዝግጅት ላይ እንዳሉ ሥጋዋን በእሳት ለማቃጠል በክፋት ተነሣሥተው ከመከሩ ማኅበረ አይሁድ ጋር ተሰልፎ የነበረውና ታውፋንያ የተባለው አይሁዳዊ የእመቤታችን ቅዱስ ሥጋ ያረፈበትን የአልጋዋን ሸንኮር ለመያዝ በድፍረት እጁን በመዘርጋቱ የእግዚአብሔር

(Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 168-169. Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality*, 117, 120-121.

[336] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 148:: *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 169:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 194::
[337] ቅዱስ ያሬድ፣ «እንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 404::



ቁጣ እንደነደደበትና በዚህም ምክንያት በመልአከ እግዚአብሔር ሰይፈ መዓት ተቀጥቶ ሁለቱም እጆቹ ከአልጋው ሸንኮር ላይ ተንጠልጥለው እንደቀሩ እንመለከታለን::[338]

ስለሆነም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ወኵሉ ዘተጽሕፈ በትግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ፤ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል» (ሮሜ 15÷4) እንዳለ፤ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም «እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለሕዝቡ በመጽሐፍ፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በመጽሐፍ ይነግራቸ ዋል» (መዝ. 86÷6) ብሎ እንደተናገረው ዛሬም ቢሆን በዘመናችን በአማናዊቷ ጽዮን በድንግል ማርያም ላይ የማይገባ የስንፍና ንግግርን የሚናገሩ ከንፈሮች፤ እንዲሁም በድፍረት ተነሣሥተው በእርሷ ላይ የማይገባና ከንቱ የሆነ ቃላትን ለመጻፍ የሚሰነዘሩ የትዕቢትና የዓመፃ እጆች ሁሉ ዕድል ፈንታቸው፣ ጽዋዓ ተርታቸው ከዖዛ ወልደ አሚናዳብ፣ እንዲሁም ከታውፋንያና ከመሰሎቻቸው ጋር መሆኑን ሊገነዘቡና ሊያስተውሉ ይገባል::

ለዚህም «በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራ ችሁም?» (ዘኍ. 12÷8)፤ «በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ዲዳ ይሁኑ» (መዝ. 30÷18)፤ «... በእግዚአብሔር አፍ ላይ ዐምፀሃልና÷ አምላክህም እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅ ህምና ... ሬሳህ ወደ አባቶችህ መቃብር አይደርስም» (1ኛ ነገሥ. 13÷21-22)፤ «ክፋውንም ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው» (ኢሳ. 10÷1-2)፤ «... አውሬውም ታላቅንም ነገርንና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው ... እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ» (ራእ. 13÷5-6)፤ «አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይ ናገሩ» (መዝ. 33÷13፤ 1ኛ ጴጥ. 3÷10-12) «እኔ እላችኋለሁ÷ ሰዎች ስለ ሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ::» (ማቴ. 13÷36-37) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎችና ምስክሮችም ናቸው::

[338] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 207-209::



ሥዕል 11፡- ታውፋንያ በመልአከ እግዚአብሔር ሰይፍ እጆቹን እንደተቀጣ

"ሰላም ለግንዘተ ሥጋኪ በእደ ሐዋርያት አርጋብ፤ በአፈወ ዕፍረት ቅድወ ዘሐሳበ ሢጡ ዕፁብ።"

("መልክዐ ማርያም"፣ ገጽ 533)




ከላይ በዝርዝር የተመለከትነውንና በታቦተ ጽዮንና በአማናዊቷ ጽዮን በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር ለማጠቃለል ያህል ታቦተ ጽዮን በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ፍልስጥኤማውያን ከተማ ተማርካ ሔዳ በቤተ ዳጎን በተቀመጠች ጊዜ ዳጎን የተባለውን የፍልጥኤማውያንን ጣዖት እንደሰባበረችውና እንደቀጠቀጠችው በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿል። (1ኛ ሳሙ. 5-6) በአንጻሩ ደግሞ አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስቀድሞ በትንቢተ ነቢያት "እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል፤ የግብፅም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ" (ኢሳ. 19÷1) "ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት" (ሆሴዕ 11÷1-2) ተብሎ በተነገረው ቃለ ትንቢት መሠረት በንጉሡ ሄሮድስ ዘመን ወደ ምድረ ግብፅ ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብራ በተሰደደች ጊዜ ኃያሉ ልጅዋ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የግብፃውያንን ጣዖታት ሽሮ፣ አምልኮተ ጣዖትን አጥፍቶ፣ የሕዝቡንም ኃጢአት በምሕረቱና በቸርነቱ ደምስሶ የክብሩ ተካፋዮች፣ የርስቱና የመንግሥቱ ወራሾች አድርጓል።[339] (ማቴ. 2÷13-23)

ይህንን ድንቅ ምሥጢር አስመልክቶ ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጽጌ ድንግል ከነገረ ድኅነት ምሥጢር ጋር በማገናዘብ ሲናገር "ታቦተ አምላክ እስራኤል ጽዮን ማርያም ዘነገደት ምድረ ኢሎፍሊ፤ ወቀጥቀጠቶ ለዳጎን ነፍሳተ ብዙኃን ማኅጐሊ፤ አሙ ነገደት ቊስቋመ በኃይለ ወልዳ ከሃሊ፤ ወድቁ አማልክተ ግብጽ መናብርተ ሰይጣን ሐባሊ፤ ወተኃፍረ ኲሎሙ ዘቦሙ አስጋሊ፤ ወደ ኢሎፍላውያን ከተማ የገባች የእስራኤል ፈጣሪ ማደሪያ የሆነች ታቦተ ጽዮን ማርያም የብዙ ሰዎችን ሕይወት የሚያጠፋ ዳጎንን ቀጥቅጣ አጠፋችው። ዳግመኛም ሁሉን በሚችል በልጇ፣ በወዳጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ወደ ቊስቋም በሔደች ጊዜ የሐሰት አባት የሆነው የሰይጣን ማደሪያ የሆኑ የግብፅ ጣዖታትም ወደቁ፣ አስማተኞችና መተተኞች የነበሩ የጣዖቱ አገልጋዮችም በሙሉ አፈሩ"[340] ብሏል። ዳግመኛም ሌላው ኢትዮጳያዊ ሊቅ በመልክዐ ማርያም ድርሰቱ "ሰላም ለመከየድኪ እለ ፈከቦን መከራ፤ እምፍርሃተ ቀተልት ሐራ፤ እንበለ አማዕን አሙ ሖራ፤ ማርያም ጽዮን ታቦተ ቃለ ጽድቅ መንፈቀ ዕሥራ"[341] ሲል ምክንያተ ድኅነት የሆነችውን እመቤታችንን አመስግኗታል።

[339] Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 49. *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 79-80።

[340] አባ ጽጌ ድንግል፣ "ሰቆቃወ ድንግል"፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 668።

[341] ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብና ዐፄ ናዖድ፣ "መልክዐ ማርያም"፣ ገጽ 531።



ሥዕል 12:- እመቤታችን ከልጇ ጋር ወደ ምድረ ግብፅ እንደተሰደደች

«አዘክሪ ድንግል ንግደት ዘምስሌኪ እንዘ ትጐይዩ ምስሌሁ እምሀገር ለሀገር በመዋዕለ ሄሮድስ ርጉም::»

«ድንግል ሆይ ርጉም በሆነ በሄሮድስ ዘመን ከእርሱ ጋር ከአገር ወደ አገር ስትሸሺ ከአንቺ ጋራ መሰደዱን አሳስቢ::»

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 191)



## 5.1.4 ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም

ከላይ በገለጥነው ምሥጢራዊ ትርጓሜ መሠረት ቅድስት ድንግል እመቤታችን ለእስራኤል ዘነፍስ የሕይወትና የደስታ ምንጭ የሆነውን መድኅነ ዓለም ክርስቶስን ያስገኘች አማናዊት ጽዮን መሆኗን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን:: ይህንን አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ ሲመሰክር «እስመ እምጽዮን ይወጽእ መድኅን፤ ወያሰትት ኃጢአተ እምያዕቆብ፤ መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፤ መርገመ ኃጢአትንም ከያዕቆብ ያስወግዳል» (ሮሜ 11÷26) በማለት አስረግጦ ተናግሮአል:: ጽዮን የሚለው ቃል ትርጉሙ አምባ፣ መጠጊያ፣ መሸሸጊያ ማለት ነው ብለናል:: በዚህም መሠረት አማናዊቷ ጽዮን እመቤታችንም ጸወነ ሥጋ፣ ጸወነ ነፍስ፤ ጸወነ ጻድቃን፣ ጸወነ ኃጥአን ናት::(342)

ይህ ታላቅ የምሥራች ቃል መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ዓለምን (የሰው ልጆችን) በተስፋ ትንቢት በኀበኝ ጊዜ በነቢዩ በቅዱስ ዳዊትና በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ የተናገረው አምላካዊ የበረከት ቃል ነው:: (መዝ. 13÷10፤ ኢሳ. 59÷20) መጻሕፍት አምላካውያት በዘመነ ሐዲስ በወልደ እግዚአብሔር የተፈጸመው የድኅነተ ዓለም ሥራ (ሐዲስ ተፈጥሮ) አስቀድሞ በተለያየ ኅብረ አምሳል የተመሰለውና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተነገረው አምላካዊ ተስፋ ፍጻሜ መሆኑን በመተባበር ይመሰክራሉ:: (ዕብ. 1÷1-2፤ ማቴ. 5÷17) ስለሆነም ለዚህ አምላካዊ የቤዛነት ሥራ ልዩ መሣሪያና ምክንያተ ድኅነት የሆነችው ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ከተገለጠችባቸው ዐበይት ኅብረ አምሳል መካከል አንዱና ዋነኛው «ጽዮን» ናት::

(342) ቅዱስ ያሬድ [St. Yared]፣ "ጾመ ድጓ" ["Soma Deggua,"] *Patrologia Orientalis* ed. F. Graffin (Paris: Librairie de Paris, 1966), 215. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gascha], *መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 374:: ቅዱስ *ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ* 92:: ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ ገጽ 747፣ 752::

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸው "ጽዮን" የሚለው ልዩ መጠሪያ ስያሜ ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን ያመለክታል:: እነዚህም:- የዳዊት ከተማ (1ኛ ሳሙ 5÷7-10)፣ የጽዮንን ተራራ (መዝ. 2÷6)፣ እንዲሁም ታቦተ ጽዮን (1ኛ ሳሙ. 5÷1-8) ናቸው:: ጽዮን የሚለው ስያሜ ለእስራኤል ዘሥጋ አምባ፣ መጠጊያ፣ መሸሸጊያ የሆነችውን የዳዊት ከተማን፣ እንዲሁም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በጸጋ የሚያድርባትንና በረድኤት የሚገለጥባትን ታቦተ ጽዮንን እንደሚያመለክት በታቦተ ጽዮንና በአማናዊቷ ታቦት በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር በስፋት በገለጽንበት ክፍል አይተናል::

ይህንን አስመልክቶ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ቸሩ አምላክ የድኅነተ ዓለምን ተስፋ አስቀድሞ ሲያናግር "ኪነ ተሰየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ በጽዮን በደብረ መቅደሱ፤ እኔ ግን በላያቸው ላይ ንጉሥ ሆኜ ተሾምኩ፤ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ" (መዝ. 2÷6) ብሏል:: በዚህም ቃለ ትንቢት መሠረት ጸወነ ሥጋ፣ ጸወነ ነፍስ፤ ጸወነ ጻድቃን፣ ጸወነ ኃጥአን እመቤታችን ድንግል ማርያም ሰማያዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅፀኗን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቤተ መቅደስ አድርጎ ተመስግኖባታልና ደብረ መቅደሱ ትባላለች::[343]

የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍተ ውዳሴያትም "ድንግል እጽንነት ርእሳ ወንገሰ ከርሣ ወትሰምዕ ቅዳሴ መላእክት፤ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም እግዚእ ስብሐት፣ እግዚእ ውዳሴ የሆነውን እግዚአብሔር ወልድን በፀነሰች ጊዜ ራሷን ወደ ማኅፀኗ ዘንበል አድርጋ ቅዳሴ መላእክትን ትሰማ ነበር" በማለት ይመሰክሩላታል:: ምክንያቱም በማኅፀኗ ያደረው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ተብለው ዘወትር ከሚመሰገኑት ከሦስቱ አካላት ማለትም ከቅድስት ሥላሴ አንዱ አካል ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ነውና:: (1ኛ ጴጥ. 2÷6፤ ኢሳ. 28÷16)

(343) *መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 29::*



ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም አማናዊት ጽዮን ተብላ በምሥጢር መጠራቷ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ግንኙነት ሲገልጥ "ወጽአ ዐቃቢ ሥራይ እምኀበ አብ እምጽርሐ አርያም:: ወድኅነት ተፈክበተ በሀገረ ዳዊት እንተ ስማ ጽዮን:: ወተፈጸመ ዘተብህለ ወኮ ይሁብ ወድኅነተ እምጽዮን ለእስራኤል::"[344] በማለት ምሥጢራዊ ትርጓሜውን አብራርቶና አፍታቶ አስረድቷል::

ከላይ እንደገለጥነው በምሥጢራዊ ፍቺውና ትርጉሙ አማናዊት ጽዮን የተባለችው ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም መሆኗን ተመልክተናል:: ይሁን እንጂ ጽዮን የተባለችው የዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም ብቻ እንጂ እመቤታችን ጽዮን ልትባል አይገባም የሚሉ አይታጡም:: በመሠረቱ ጽዮን ማለት አምባ፣ መጠጊያ፣ መሸሸጊያ ማለት ነው:: እመቤታችን ጽዮን መባሏም አዳምና ሔዋን በምክረ ከይሲ ተታልለው፣ ሕገ እግዚአብሔርን ተላልፈው፣ የሞት ሞት ተፈርዶባቸው፣ ከክብር ቦታ ከገነት ወጥተው፣ በመንጸፈ ደይን ወድቀው፣ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቁ ለድኅነተ ዓለም ስንቀ ተስፋ ሆና የተሰጠች አምባና መጠጊያ፣ መሸሸጊያና መጽናኛ ስለሆነች ነው:: (ገላ. 4÷4፤ ዘፍ. 3÷15) ታላቁ ሊቅ ቅዱስ አባ ሕርያቆስም እመቤታችንን ባስገነበት ቅዳሴው "እንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት፤ ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ" ሲል ያመሰገናት ስለዚህ ነው::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱሳት መጻሕፍት ጽዮን ተብላ በምሥጢር እንደተጠራች ከላይ ከገለጽነው በተጨማሪ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር 131÷13 ላይ "እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤ ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ:: ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም:: ዝየ እኀድር እስመ ኀረይክዋ፤ እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና÷ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና÷ እንዲህ ብሎ:- ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ::"

(344) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"]* ፣ ገጽ 379::

በማለት ተናግሮአል። በዚህ ገጸ ንባብ ውስጥ ጽዮን የሚለው ስያሜ የእመቤታችን ትክክለኛ መጠሪያ መሆኑን መረዳት እንችላለን። ምክንያቱም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ማደሪያው ትሆነው ዘንድ ከአንስተ ዓለም ሁሉ ለይቶ ለእናትነት የመረጣትና ለድኅነተ ዓለም መሣሪያነት ያዘጋጃት አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ብቻ ናትና። (መዝ. 45÷4፤ ሉቃ. 1÷28-42) ዳግመኛም ለልጁ ማደሪያው ትሆነው ዘንድ ማለትም ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማኅፀኗን ዓለም አድርጎ ያድርባት ዘንድ ለተዋሕዶ እንደመረጣት በግልጽ ይመሰክራል።

ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት እመቤታችንን ከምድራዊቷ ጽዮን ከኢየሩሳሌም ሲለያት «ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት» በማለት ገልጾአል። ምክንያቱም ምድራዊቷ ጽዮን (የዳዊት ከተማ) ዘለዓለማዊት አይደለች ምና። ጌታችንም በቅዱስ ወንጌል «ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።» (ማቴ. 24÷35) በማለት ይህ የሚታየው ሰማይና ያለንባት ምድርም ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ማደሪያ አለመሆናቸውን፤ ይልቁንም በዕለተ ምጽአት ከመኖር ወደ አለመኖር የሚያልፉ መሆናቸውን ገልጾ አስረድቶናል። (2ኛ ጴጥ. 3÷10-13፤ ራእይ 21÷1-2)

በመሆኑም ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት በምሥጢር የገለጣት ይህቺ ዘለዓለማዊት ጽዮን ቅድመ ዓለም የነበረ፣ ማዕከለ ዓለም ያለ፣ ድኅረ ዓለምም የሚኖር አልፋና ኦሜጋ የሆነው አምላክ በኩነት ያደረባት ማለትም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው የሆነባት የዘላለማዊ ንጉሥ ክርስቶስ እናቱ አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ናት። ዳግመኛም እመቤታችን ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ስትባል መኖሯንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርሷ የነሣው ሥጋ ለዘለዓለም የሚኖር ሕያው ባሕርይ መሆኑን ያስረዳል።[345]

ከዚህም ጋር ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር 86÷5 ላይ «እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ። ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ። ወውእቱ

[345] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 431-432።



ልዑል ሣረራ፤ ሰው እናታችን ጽዮን ይላል÷ በውስጥዋም ሰው ተወለደ፤ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።» በማለት ተናግሮላታል። የዚህ ቃለ ትንቢት ምሥጢራዊ ፍጻሜው መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ከእመቤታችን በተዋሕዶ ሰው ሆኖ ተወልዷልና፤ እመቤታችንንም በንጽሕና፣ በቅድስና፣ በኀቱም ድንግልና አጽንቷታልና፤ ከቀኝ ጎኑ በፈሰሰው ማየ ገቦ ተጠምቀው፣ በመንፈስ ልደት የከበሩ ምእመናነ ሐዲስ በሙሉ ድንግል ማርያም እናታችን፣ መድኃኔዓለም ክርስቶስ አባታችን ገነተ መንግሥተ ሰማያት ርስታችን ብለው በማመን ጸንተው ይኖራሉ ማለት ነው።[346] በዚህም መሠረት በተዋሕዶ ከእርሷ ሰው ሆኖ የተወለደውን የአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ወልድን እናት ድንግል ማርያምን በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ እናታችን ብለው የሚጠሯት አማናዊት ጽዮን መሆኗን ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ገልጾ አስረድቷል።

በአዲስ ኪዳንም ከመልአኩ ከቅዱስ ገብርኤል ዜና ብሥራት በኋላ እመቤታችን ኤልሳቤጥን በጎበኘቻት ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ኤልሳቤጥ አድሮ የገለጠውን አማናዊ የምስክርነት ቃል በሉቃስ 1÷39-44 ላይ «... ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ። በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት። በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች፡- አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና።» ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን።

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ይህንን ምሥጢር ሲተረጉሙ «ዮሐንስ ሰገደ ውስተ ከርሠ እሙ» በማለት ገልጸውታል። ይህም ማለት መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ የእናቱን የቅድስት ኤልሳቤጥን ማኅፀን መቅደስ አድርጎ በእመቤታችን ማኅፀን ለተፀነሰው ለጌታችን ለኢየሱስ

[346] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 621።

ክርስቶስ የአምልኮ ስግደት፣ ለወላዲተ አምላክ ለቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ የጸጋ ስግደት ሰገደ ማለት ነው::

ከላይ እንደተመለከትነው ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተመላች የቅድስት ኤልሳቤጥ ልጅ መጥምቁ ዮሐንስ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ስለነበረ የእመቤታችንን የሰላምታ ድምፅ በሰማ ጊዜ በደስታ ዘሎአል:: በዚህም ለእመቤታችን የጸጋ ክብር ሰጥቷል:: እንግዲህ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን ከላይ በገለጽነው ዓይነት ምስጋና የሚያከብሯትና የሚያመሰግኗት መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች መሆኑን ይገነዘቧል:: እርሷም በሉቃስ 1÷48 ላይ "እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ብላ እንደተናገረችው በልጇ፣ በወዳጇ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን፣ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ፣ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ በጥምቀት ተወልደን፣ በአማላጅነቷና በቃል ኪዳኗ የምናምንና የምንታመን ክርስቲያኖች ሁሉ ጸወነ ሥጋ፣ ጸወ ነፍስ የሆነችውን እመቤታችንን ብፅዕት ነሽ፣ ንጽሕት ነሽ፣ ጽንዕት ነሽ፣ ንዕድ ክብርት ነሽ እያልን ዘወትር እናመሰግናታለን:: በዚህም አማናዊ ምስጋናችን መንፈስ ቅዱስን ከተመላች ከቅድስት ኤልሳቤጥ፣ ከጸያሔ ፍኖት ከቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ እንዲሁም ከሰማያዊው መልአክ ከቅዱስ ገብርኤል ጋር እንተባበራለን::

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው አቢዳራ ቤቱን ለታቦተ ጽዮን በፈቃዱ እንደሰጠና ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ በበረከት እንደጎበኘ፤ ንጉሠ እስራኤል የሆነው ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም አምኃ ውዳሴውን በታቦተ ጽዮን ፊት እንዳቀረበና በዚህም አምላከ እስራኤል እግዚአብሔር ሕይወቱን ፍጹም እንዳከበረለት ተመልክተናል:: ዳግመኛም ቅድስት ኤልሳቤጥ ለአማናዊቷ ጽዮን ለድንግል ማርያም ቤቷን እንደከፈተችና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ ልዩ የሆነ ቃለ ውዳሴ እንዳቀረበችላት አይተናል:: ከዚህም ጋር እመቤታችን የድኅነተ ዓለም ተስፋ በተፈጸመበት በቀራንዮ መስቀል አጠገብ በፍቁረ እግዚእ በቅዱስ ዮሐንስ



ወንጌላዊ አማካይነት ለዓለም ሁሉ እናት ሆና በጸጋ ተሰጥታለች:: በመሆኑም ይህ ታማኝ ሐዋርያ ፍቁረ እግዚእብሔር (የእግዚአብሔር ወዳጅ) የሆኑትን አቢዳራን፣ ቅዱስ ዳዊትንና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተመላች ቅድስት ኤልሳቤጥን አብነት አድርጎ ቤቱን ለፈጣሪው እናት ለድንግል ማርያም በፈቃዱ ሰጥቷል:: (ዮሐ. 19÷27) እንግዲህ እኛም እነርሱን አብነት አድርገን ቤት ልቡናችንንና ሕይወታችንን ጸወነ ሥጋ፣ ጸወነ ነፍስ፤ ጸወነ ጻድቃን፣ ጸወነ ኃጥአን ለሆነችው ለቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ከፍተን የእርሷ ጣዕመ በረከት፣ ጣዕመ ፍቅርና ጣዕመ ውዳሴ፤ እንዲሁም የልጇ የወዳጇ የመድኃኔዓለም ምሕረትና ቸርነት እንዲያድርብንና እንዲበዛልን መዘጋጀት ይገባናል::

## 5.1.5 ሐውልተ ስምዕ ዘኢያሱ (የኢያሱ የምስክር ሐውልት)

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በሦስት ወገን ማለትም በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና የተሸለመችና ያጌጠች፤ አንድም በሐልዮ (በማሰብ)፣ በነቢብ (በመናገር)፣ በገቢር (በመሥራት)፣ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ኅትምት የመሆኗን ምሥጢር በኢያሱ የምስክር ድንጋይ መስለው አስተምረዋል:: ዳግመኛም ኢያሱ ከእስራኤል ዘሥጋ ጋር የተማማለባት ድንጋይ ባለ ሦስት ገጽ መሆኗ እመቤታችን በሦስት ወገን ዘለዓለማዊት ድንግል (ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ፤ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ) ለመሆኗ ምሳሌ ነው::[347]

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ለአማናዊው መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የነበረው ኢያሱ በዚህች ድንጋይ አማካይነት ስሙ እንደታወቀ ሁሉ፤ እንደዚሁም ድኅነተ ሥጋን፣ ድኅነተ ነፍስን የሚሰጠው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ከእመቤታችን በተወለደ ጊዜ ለዓለም ሁሉ ታውቋልና:: ለዚህም "እነሆም÷

[347] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 94-95::*